# አረ በኢትዮጵያ አምላክ! በሕግ፣ ወድቃ በተነሳችው ሠንደቃችን!!
# ወያኔዎች! ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮን) ፍቱልን እባካችሁ!!

ከአያልነሽ

[1]



**ቴዎድሮስ (ቴዲ አፍሮ )ይፈታ!!**

**ቴዎድሮስ (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!!**

**ቴዎድሮስ (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!!**

ምን ዓይነት ዕርጉም ባላንጣ ነው የገጠመን ጃል! ደግሞ በቴዲ ላይ?
ቂመኛው ወያኔ በሙዚቃና በግጥም ተሰጥዖው ዝነኛና ዓለምን ያስደመመው ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮን)፣ እንደተለመደው በቂም የተለበደ የሃሰት ክስ መሥርቶ ዘብጥያ አውርዶታል። በቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ላይ ወያኔ የከፈተበት የሃሰት ውንጀላ፣ ከዓመት በፊት ''አንድ የጎዳና ተዳዳሪ ገጭቶ በማምለጥ፣ ያለ መንጃ ፈቃድ በማሽከርከርና ተጎጅን ባለመካስ የሚል'' ሲሆን ቴዴ ለዚህ በወያኔ ለተቀነባበረበት በቂም የተበከለ የሃሰት ክስ በወቅቱ (ከዓመት በፊት) ክሱን መሰረተ ቢስ በማለት ውድቅ አድርጎት ነበር። ቴዲ ለዚህ ለተቀነባበረበት የሃሰት ክስ ያኔ በጋዘጠኞች ተጠይቆ የሰጠው መልስ እንዲህ የሚል ነበር።

> ''እኔ ይህ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት በተፈጸመበት ቦታ አልነበርኩም፣ በተጨማሪም ክቡር የሆነውን ሰው ህይወት ገድዬ ወይም ገጭቸ የምሸሸ ሰውም አይደለሁም። ይልቁንም ክቡር በሆነው የሰው ሕይወት ላይ ይህንን መሰል ከባድ ወንጀልና ድርጊት ፈጽመሃል ተብሎ መከሰሴ ክብሬን የሚነካና ሰብዕናዬንም የሚያጉድፍ ነው...'' ብሎ ነበር

ይህንን ተወዳጅና እያስረቀረቀ በሚያወጣው ድምፁ በርካታዎችን በስሜት ማዕበል ውስጥ ያሰመጠውንና ኢትዮጵያን በግጥሙ ይዘትና በመረዋ ቅላፄው ለዓለም እያስተዋወቀ ያለውን ወጣት አርቲስት ቴዎድሮስ ካሣሁንን፣ ወያኔ አድብቶ ሊበቀለው ቆርጦ ተነስቷል። ለምን? መልሱ ግልፅና እንደ ሰማይ የጠራ ነው። ወያኔ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ ያለው ያመረረ ጥላቻና የበቀል ስሜቱ ነው። ግን ለምን? ለምን በኢትዮጵያ ላይ? አሁንም እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ሁሉ ደግሞ ደጋግሞ ሊጠይቀውና ሊያቃጭልበት የሚገባ ጉዳይና ጥያቄ ነው።
ወያኔ ይህ በቂምና በሸር ያደገበት አባዜው የማይለቀውና የተጣባው በሽታ በመሆኑ በዓመቱ የሃሰት ክሱን እንደገና አድሶና ደርቶ በማቅረብ ቴዎድሮስ ካሣሁንን በቃሊቲ እሥር ቤት አሥሮት ይገኛል።

የተከበራችሁ አንባቢዎች ሆይ !

- ወያኔ ያሰረው ቴዲን ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን ነው።

---

[1] የፎቶዎች ምንጭ Reggaephotos.de

- ወያኔ እስካሁን አምርሮ የሚገድለው፣ አሁንም እየገደለና እያስደደ ያለው ኢትዮጵያዊነትን ነው።
- ወያኔ ቂሙ አሁንም ከቴዲ ጋ አይደለም፤ ወያኔ ቂሙ ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያዊነት ጋር ነው።
- የወያኔ ችግር የቴዲ ታዋቂ መሆን ሳይሆን፣ ቴዲ ታዋቂነትንና ተወዳጅነትን ያተረፈለት፣ እያስረቀረቀ የሚያወጣው ድምፁና ኢትዮጵያዊነትን ክፍ የሚያደረግበት የግጥም ችሎታው ነው።
- ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) አሁን የታሰረው ወያኔ የፈጠረው የሃሰት ወንጀል ዕውነት ሁኖ ሳይሆን በ1997 ዓ.ም የለቀቀው "ያስተሰርያል" የሚለው የሙዚቃ አልበሙና በዓለም ደረጃ በአንዴ ተወዳጅነትን ያተርፈለትና የተነገረለት የሙዚቃ ስልቱ ነው።
- በቴዲ ላይ የተመሰረተው ክስ በኢትዮጵያውነት ላይ እንጂ አሁን ወያኔ በደረተው የስም ማጥፋትና የሃሰት የውንጀላ ድርሰት አይደለም። ወዘተ ወዘተ ወዘተ....

ስለዚህ ቴዎድሮስ መፈታት አለበት። ለቴዲ አፍሮ መታሰርና መንገላታት ተጠያቂው ወያኔ ነው። ቴዲ በስርቅርቅ ድምጹ የተጫወተልንና ያበረከትልን ሙዚቃ፣ ለወያኔ የጎን ውጋት ነው፤ "ሸመንደፈር"። የወያኔን የጎጠኝነት ዛር የሚያቆስልና የሚሸረሽር ነው፤ "ሸመንደፈር"። የወያኔን የዘር ህድሞ የሚደረምስ ነው፤ "ሸመንደፈር"። እስቲ የቴዲን ስጦታ ሸመንደፈር ከሚለው ሙዚቃ ውስጥ ትንሽ ልበላችሁ።

ሼመንደፈር! ሼመንደፈር ሸመንደፈር
አሆሆ አሆሆ ሼመንደፈር! ሼመንደፈር! ሼመንደፈር!
አሆሆ! አሆሆ! አሆሆ! አሆሆ! ሼመንደፈር! ሼመንደፈር!
ሼመንደፈር!
አዛና አለ መስጊድ ልትነጋ ምድር፣
ልሂድ ሸህ መንደፈር ልሳፈር ባቡር፣
በእንግድነት መጥታ ከሸገር ሐረር፣
ልቤን ይዛው ሄደች ወደሩቅ ሀገር፣
ሼመንደፈር!



ተዋድዶ ያለበት እሥላም ክርስቲያኑ፣
ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ፣
አንችም በሐይማኖትሽ፣ እኔም በሐይማኖቴ፣
መኖር እንችላለን አይጠበንም ቤቴ።
ሼመንደፈር!
ሸገር አዲስ አበባ አንች ያለሸበት፣
ራጉዔል አይደል ወይ የአንዋር ጎረቤት፣
ቅዳሴና አዛኑን አጥር ቢለያቸው፣
ፈጣሪ ከሰማይ አንድነት ሰማቸው(በፍቅር እያቸው)

ለፀረ-ኢትዮጵያው ወያኔ ''ሼመንደፈር'' እንዴት ይጥመዋል? ሼመንደፈር ሙዚቃ ወያኔን እንዴት ሊያስደስት ይጠበቃል? የቴዲ አፍሮ ''ሼመንደፈር'' ሙዚቃ መላውን ኢትዮጵያዊ አስደምሞ ምርኮ አደረገ እንጂ፣ መለስንና ቡድኑን እንዴት ሊማርክ ይችላል? ለፀረ-ኢትዮጵያው ወያኔ ደግሞ ባይገባው፣ የሚያስገርም፣ የሚያስደንቅ ሊሆን አይችልም። ወደድንም ጠላንም ይህ ከደደቢት የፈለሰ የወያኔ ቡድን ኢትዮጵያን አይወድም፣ እንዲወድም አይጠበቀም፤ አራት ነጥብ።
የቴዎድሮስ በቃሊቲ እንዲታጎር መደረግ ደግሞ ከወያኔ ፀረ-ኢትዮጵያዊነት የሚመነጭ እንጂ ቴዲ ባለነበረበት ቦታና በማያውቀው ጉዳይ ''ሰው በመኪና ገጭተኃል'' የሚል የሃሰት ክስ ''ከብት ባልዋለበት ኩበት ለቀማ'' ዓይነት የወያኔ የብቀላ እርምጃ ነው። የቴዲ አፍሮ መታሰር ኢ-ፍትኃዊ ነው። ቴዎድሮስ ካሣሁን የታሠረው በተባለው በወያኔ የፈጠራ ክስ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን በማቀንቀኑ ነው። ስለዚህ ወያኔዎች ቴዲዬን ፍቱልን! ይህ የበቀል እርምጃ ለማንም አይበጅም። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ደግሞ እሴታችን ቴዲ አፍሮ እንዲፈታ መጮህ፣ መሰለፍና ድምፁን ማስተጋባት አለበት። እሴቶቻችንን እያሳሰርን ዝምታ እስከመቼ?

ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!!
ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!!
ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) ይፈታ!!

የህዝብ ድምጽ ይከበር! የታሠሩ የፓለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!
ቼር ይግጠመን!
ሚያዚያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም
አፕሪል 24/ 2008